# ዛሬ እንኳን ነፍስ እወቅ (ለግንቦት 7)

ደም እያሸተተ ሀገር ከቀረናው
ከሰፈር አመድ ላይ ከሚንከባለለው
ከአድኋዊ ከአድመኛ በዘር ከጠበበ
በጎጥ ፖለቲካ ናላው ከታወረ
አንድነት ከጠላ ፍቅር ከገደበ
በጎሳ በክልል እራሱን ካጠረ
አትጠጋ ብየ ነግሬህ ነበረ::
አልሰማም አልህና ጣሬን አበዛህው:
ተስፋየን አጨለምህ ስሜቴን ጎዳህው ::
በሰራህው ስህተት
ምኞቴ በውስጤ ሞቶ ተቀበረ:
ህልሜ ቅዠት ሆነ ተስፋየ ጨለመ
ቅስሜም - ተሰበረ::
ኢትዮጵያዊነትን አምርሮ ከጠላ
በዘር ፖለቲካ ከተቃኘ ሁላ
በጋራ እሰራለሁ
ብለህ እንዳታስብ መክሬህ ነበረ:
አልሰማ ብለኸኝ
የፈራሁት ሁሉ ይደርስ ጀመረ
ይኸው - እያደረ::
"ዘር ከልጓም ይስባል" የሚባለው ብሂል ቀልድ እየመሰለህ:
ምክሬን ከቁብ ሳትቆጥር
ውትወታየን ገፍተህ ከጎሰኛ አብረህ:
ጆሮ አልሰጥ ብለኸኝ በስሜታዊነት የጀመርኸው መንገድ
የት እንዳደረሰህ:
የህልም ሩጫህን ላፍታ ገታ አርግና
አስተውል - ቆም ብለህ::
ወዳጅ ከጠላት ለይ አትሁን ተላላ:
ከነማን ጋር መምከር ከነማን መጠንቀቅ
እንደሚገባ አስላ::
የበሰበሰ አንጎል አክማለሁ ብለህ
ጊዜህን አትግደል:
የማይገናኙ አስተባብራለሁ
አትበል - አስተውል::
ሀገርን ለማዳን ህዝብን ለመታደግ
ከግቡ ለመዝለቅ:
ወዳጅ ከጠላት ለይ
ዛሬ እንኳን - ነፍስ እወቅ::